# አካፋን አካፋ እንላለን!!!

ሀገራችን ኢትዮጵያ በጠባብ ዘረኞች መዳፍ ስር ከወደቀች እነሆ ከሁለት አስርት አመታት በላይ ተቆጠሩ። ህዝባችንም ቢሆን በዋነኛነት በዘር እንዲከፋፈል ተደርጎ እርስ በርሱ እንዳይተማመን ይልቁንም በጠላትነት እንዲተያይ ከመደረጉም ባሻገር በፖለቲካና በማህበራዊ ጉዳይ በገዛ ሀገሩ ባዕድ እንዲሆን ተደርጓል።በኢኮኖሚውም ቢሆን ኑሮው ዕለት፥ዕለት እያሽቆለቆለ በልቶ ማደርን እንደትልቅ ፀጋ ከሚቆጥርበት ዘመነ ፍዳ ላይ ይገኛል።

የፅሑፌ አላማ ሀገራችን ኢትዮጵያ የገባችበትን አዘቅት እና ህዝቦቿ የሚገኙበትን ሰቆቃ ለመዘርዘር ሳይሆን ከዚህ አስከፊ ሁኔታ ሀገራችንና ህዝቦቿ እንዳይወጡ የየበኩላቸውን አስተዋፅኦ ከሚያደርጉ ሰንኮፎች መካከል በአንዱ ዙሪያ ያለኝን አስተያየት ለማካፈል ነው።

የወያኔን ዕድሜ ከሚያራዝሙ በርካታ ምክንያቶች መካከል ጭንጋፍ /ምቁር/ ፖለቲከኞችና ፍሬ አልባ ድርጅቶቻቸው በዋናነት ይጠቀሳሉ።

እነዚህ ጭንጋፍ /ምቁር/ ፖለቲከኞች በሀገር ቤትም ከሀገር ቤት ውጪም በተለይ በአውሮፓና በዩ ኤስ አሜሪካ ይገኛሉ።የሀገር ቤቶቹ በአብዛኛው በምርጫ ሰሞን በወያኔ ተጠፍጥፈው የሚሰሩ አልያም ራሳቸው እንደ አሸን ፈልተው ከምርጫው ጋር አብረው የሚከስሙ ሲሆን ከዛ ውጪ ያሉትም ቢሆን የህዝብ አመኔታ የሌላቸውና መዋያ ባጡ አዛውንቶች የሚዘወሩ ፍሬ አልባ ሆነው እናገኛቸዋለን።ይህ ማለት ግን በሀገር ቤት ከወያኔ ጋር እየተላተመ ብሎም መስዋዕትነት እየከፈለ የሚታገል ድርጅት የለም ማለት አይደለም።

በሌላ በኩል በህዝባችን ቁስል ላይ ጥዝጣዜን እየጨመሩ ከሚገኙት መካከል ውጪ ሀገር የሚኖሩ ነፍስ-አልባ ተንቀሳቃሽ ሬሳዎች ሲሆኑ እኚህ የጨነገፉ ፖለቲከኞች "ኢትዮጵያን ነፃ እናወጣለን" እያሉ ፍሬ-አልባ ድርጅቶችን በማቋቋም በህዝብ ስም የሚነግዱ፣በነፃነት ስም እየማሉ ነፃ ያልወጡ፣በስደተኛ ወንድሞቻቸው ስቃይ የግል ጥቅማቸውን የሚያሳድዱ፣የሚሰርቁ፣የሚዋሹ፣ስደተኛ ሴት እህቶቻችንን የሴሰኝነታቸው ማራገፊያ የሚያደርጉ ሲሆን "ሰው መሳይ በሸንጎ" እንደሚባለው ወድቆ በተነሳው ባንድራችን በየአደባባዩ ሲምሉ፣ስለሀገር አንድነት እና ስለህዝቦቿ ፍትህ ማጣት ሲያወሩ ኤሎሄ ከማለት አልፈን ብዕር እንድናነሳ አስገድዶናል።

ለዛሬ መነሻዬን የአውሮፓ እምብርት ከሆነችው ጀርመን አድርጌአለሁ። *(በዚህ አጋጣሚ ውድ አንባብያን ሆይ! በስራ ምክንያት ዩ ኤስ አሜሪካ በየጊዜው የምሄድ በመሆኑ በአሜሪካም ያየሁትንና በቂ ማስረጃ ያገኘሁበትን በቀጣይ እትም አቀርበዋለሁ)።*

በጀርመን ከሚገኙ ፍሬ-አልባ የ"ፖለቲካ" ድርጅቶች መካከል እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ራሱን የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር በማለት ሲጠራ ቆይቶ በመጨረሻም በሦስት አንጃዎች ሲከፈል ለራሱ "የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ" በሚል ሻማ አብሩልኝ፥ኬክ ቁረሱልኝ ሳይል የዳቦ ስም ስላወጣው ድርጅትና አሳፋሪ ተግባሩ ይሆናል።

ራሱን የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ እያለ የሚጠራው ፍሬ-አልባ የ"ፖለቲካ" ድርጅትን በዋናነት የሚመራውና የሚያስተዳድረው ጭንጋፍ /ምቁር/ ፖለቲከኛው የመቶ

አለቃ ልዑል ቀስቅስ ሲሆን የጥቅም ተጋሪውና የግብር አቻው መቶ አለቃ ጥላሁን ጉደታም ይገኙበታል።በእርግጥ እነዚህ ሁለት ግለሰቦች በአንድ ወቅት በጀርመን በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ላይ ባደረሱት ያታዊ ጥቃትና የገንዘብ ብዝበዛ ምክንያት በኢንተርኔት ፔቲሽን ከተሰበሰበ እና የሰው ምስክሮች ተዘጋጅተው ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት ሊያቀና ሲል ታላላቅ ኢትዮጵያውያን ሽማግሌዎች በመሀል በመግባት ጉዳዩ በሽምግልና እንዲፈታ ተደርጓል።ይሁን እንጂ ካለፈ ስህተታቸው ያልተማሩትና በሀገርና በነፃነት ስም የሚነግዱት ጭንጋፍ /ምቁር/ ፖለቲከኞች ዛሬም በጀርመን በሚገኙ የፖለቲካ ጥገኝነት ጠይቀው ምላሻቸውን በሚጠባበቁ ኢትዮጵያውያን ላይ እያደረሱ ያሉትን ግፍና መከራ መልኩን በመቀየር እንደቀጠሉበት ይገኛል። ለማጭበርበሪያነት ከሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች መካከል በየአደባባዩ እና በየአዳራሹ አንዴ በኤርትራ ጦር አለን ለዛ ጦር መርጃ ብር ለግሱ ሲሉ ሌላ ጊዜ ደግሞ ጦራችን የሚገኘው በኢትዮጵያ ወያኔን እየተፋለመ ነውና እርዱን እያሉ የሚያወሩት ተረት ነው።በእርግጥ በአንድ ወቅት በዚሁ በጀርመን የሚገኝ የሲቪክ ማህበር ባዘጋጀው ስብሰባ ላይ



አቶ ጥላሁን ጉደታ

(ፌብሯሪ 09, 2013 ዓ.ም. በኑረንበርግ ከተማ በተዘጋጀ አንድ ስብሰባ ላይ በአንድ በኩል አስመራ ምንም ግንኙነት የለንም ሲሉ በሌላ በኩል አስመራ የሚገኘው መአዛ ጌጡ መሪያችን ነው በማለት የሚጋጭ መልስ ከመስጠታቸውም ባሻገር አንዳንድ ቦታ የሚናገሩት ጠፍቷቸው ሲደናገሩ ከመታየቱም በላይ ከተሰብሳቢው ከፍተኛ ተቃውሞ ተሰንዝሮባቸዋል።)

"እውነቱ ይውጣ፥በግንባር ላይ ከሚገኘው አርበኞች ግንባር ጋር ግንኙነት ያለው ማነው?" በሚል ከተሰብሳቢው ሲጠየቅ መቶ አለቃ ጥላሁን ጉደታ ይይዝ ይጨብጠውን ማጣቱን ያስተዋልኩት በኑረንበርግ ከተማ የሚኖር ወዳጄ በስብሰባው ላይ የተቀረፀውን ቪዲዮ ልኮልኝ ስመለከት ነበር።ጦር ሳይኖራቸው ስለፍልሚያ የሚዘምሩ፣የራሳቸው ያልሆነን ድርጅት ከትግል ሜዳ አውጥተው መሀል አውሮፓ አምጥተው ሊሰነቅሩት የሚሹ፣በስሙ የሚለምኑ ነገር ግን አርበኛውን የማያውቁ የስካርና የሴሰኝነት አርበኞች ናቸው እንግዲህ የኢትዮጵያን የዲያስፖራ ፖለቲካ እየተፈታተኑት ያሉ።

በነገራችን ላይ ይህ ራሱን "የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ" እያለ የሚጠራው ድርጅት የድርጅትን ስያሜ ብቻ ሳይሆን የግለሰቦችንም ፅሁፍ ሳይቀር ይሰርቃል።

መቼም ወግ አይቀርምና "ጎህ" የሚል የድርጅት ልሣን አዘጋጀን በማለት አባላቱን በ10 ዩሮ እንዲገዙ ማስገደድ ከጀመሩ ሰነባብተዋል።እናም የዚህ "ጎህ" የሚባል ጥራዝ (መፅሔት ለመባል የሚያበቃ አንዳችም ነገር ስላላገኘሁበት ጥራዝ ብዬዋለሁ) ዋና አዘጋጅና የነ ልዑል ቀስቅስ ተባባሪ የሆነው አቶ ደሳለኝ አዴላ የሚባል ግለሰብ ሲሆን በአንደኛ አመት ቁጥር ሁለት እትም ገፅ 7 ላይ "የሰማዩን እንኳን ተውልን" በሚል ርዕስ ያወጣው ፅሑፍ ርዕሱ እንኳን ሳይቀር ይዘቱም ጭምር በአቶ ደሳለኝ አዴላ  ከፍትህ ጋዜጣ ላይ ተሰርቆ የወጣ ፅሑፍ ነው።

በመጋቢት 07 2004 ዓ.ም. በታተመችው የፍትህ ጋዜጣ (ፍትህ ቅፅ 5 ቁጥር 179 አርብ መጋቢት 7 2004 ዓ.ም) ላይ ከወጡት ፅሑፎች መካከል **በአክመል ነጋሽ (የሙስሊሞች ጉዳይ መጽሔት ሲኒየር ኤዲተር) የተዘጋጀው ፅሑፍ ርዕስ "የሰማዩን እንኳን ተውልን"** የሚል ሲሆን አቶ ደሳለኝ አዴላ የተባለው የ"ኀህ መጽሔት" አዘጋጅ እንግዲህ ከዓመት በኋላ ይህንኑ ርዕስ በመስረቅ እና በአሳፋሪ መልኩ ከዛው የፍትህ ጋዜጣ (ፍትህ ቅፅ 5 ቁጥር 179 አርብ መጋቢት 7 2004 ዓ.ም) ቃል ሳይጨምር፥ቃልም ሳይቀንስ ከታዋቂው ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ (የፍትህ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ) በፍትህ ጋዜጣ ቁጥር 179 አርብ መጋቢት 7 2004 ዓ.ም **"ሲኖዶሱ እና መጅሊሱ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ማጥመቂያ?"** በሚል ርዕስ ከታተመው ፅሑፍ ቃል በቃል በመስረቅና የራሱ በማስመሰል በራሱ ስም አውጥቶታል።

አንባብያን የራሳቸውን ፍርድ ይሰጡ ዘንድ ርዕሱ የተሰረቀበትን የአክመል ነጋሽን ጽሑፍ፣ እንዲሁም ይዘቱ የተሰረቀበትን የታዋቂው ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝን ኦሪጅናል ጽሑፍንና የ"ኀህ መጽሔት" ዋና አዘጋጁ ደሳለኝ አዴላ ሰርቆ በራሱ ስም ያሳተመውን ፅሑፍ ለማስረጃነት ከዚህ በታች አቅርቤዋለሁ።ኦሪጅናሉ እና ከዓመት በፊት የታተመው የታዋቂው ጋዜጠኛ ተመስገን ፅሑፍ ላይ በቢጫ ቀለም "ሃይ ላይት" /High Light/ የተደረጉትን ፅሑፎች በሙሉ ቦታቸውን በማገለባበጥ የ"ኀህ መፅሔት" አዘጋጁ ደሳለኝ አዴላ የሰረቃቸው ፅሁፎች ናቸው።




በዚህ አጋጣሚ የሰው ፅሁፍን የራስ አስመስሎ በከፊልም ይሁን በሙሉ ማሳተም "ፕላጂያሪዝም" /Plagiarism/ ሲባል ይህም ትልቅ ወንጀል ነው። ለምሳሌ የጀርመን የመከላከያ ሚንስትር የነበሩት ካርል ቲዎዶር ሱ ጉተንበርግ የሰው ፅሑፍ በመስረቅና የራሳቸው በማስመሰል ዶክትሬታቸውን ከሰሩ ከአምስት /5/ ዓመት በኋላ ይህ ድርጊታቸው በመታወቁ የዶክትሬት ማዕረግ የሰጣቸው የባይሮይት ዩኒቨርሲቲ /University of Bayreuth/ በ 2011 ዓ.ም. የዶክትሬት ማዕረጋቸውን ሲነጥቃቸው እሳቸውም ከደረሰባቸው ጫና አንፃር ስራቸውን በፈቃዳቸው ሊለቁ ችለዋል።ታሪካዊ አጋጣሚነቱን አስገራሚ የሚያደርገው ደግሞ የተመስገንን እና የአክመልን ፅሑፍ የሰረቀው የአርበኞች ግንባር ዘቡ ደሳለኝ አዴላ በባይሮይት /Bayreuth/ ከተማ እንደሚኖር በዛው ገጽ 7 ላይ ከጽሑፉ በታች ከስሙ ግርጌ ማስፈሩ ነው።የምንቀማው ዶክትሬት ባይኖረውም እውነቱን ግን ይፋ እናወጣለን።

ጎበዝ! እንዴት ነው ነገሩ?!የድርጅት ስም ተሰርቆ፣ርዕስ እንኳን ሳይቀር የሰው ፅሑፍ ተሰርቆ፣ስደተኞች እየተበዘበዙ፣ጦር በሌለበት ስለፍልሚያ ተዘምሮ! ኧረ እስከመቼ ተዋሽቶ ይዘለቃል?!!!



ቤታቸውን እየከፈቱ ሰው ሌባ ይላሉ የስዊድን ጋዜጠኞችና...

ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም 3

ጥቂት ስለ "ሀበሻ ጀብዱ"

ተጫነ ጆብሬ መኮንን (የሀበሻው ጀብዱ መፅሃፍ ተርጓሚ ከቼክ ሪፐብሊክ) 7



በኢትዮጵያ የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን ማን ሰመነመነ?

አቶ ቡልቻ ደመቅሳ 7



# ፍትህ

ቅፅ 5 ቁጥር 179 አርብ መጋቢት 7 2004 ዓ.ም www.fetehe.com Addis Ababa-Ethiopia ዋጋ 7.00 ብር

## ሲኖዶሱ እና መጅሊሱ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ማጥመቂያ? 5



የኢትዮጵያ ቡና ክለብ ካምፑን በሶስት ቀናት እንዲያፈርስ ታዘዘ 15

የገዳማትና አድባራት አሥተዳዳሪዎች ሀገረ ስብከቱ ከስራና ደመወዝ አገደን አሉ 15

የኢትዮጵያ መንግስት በኤርትራ ላይ ወታደራዊ ጥቃት ሰነዘረ 15

በቤሩት የጭካኔ ተግባር የተፈፀመባት ኢትዮጵያዊት ራሷን አጠፋች ተባለ 15



"ተገልቢጥናዋ ተገልበጣ"

ዓምደም ገብረስላሴ ኣስፈሃ ከመቐለ (የደምፀ ወያኔ ጋዜጠኛ የነበረ) 4

የሰማዩን እንኳ ተዉልን!

አክመል ነጋሽ (የሙስሊሞች ጉዳይ መጽሔት ሲኒየር ኤዲተር) 9



ቸሽገብሩ የሞተችለት ነፃነትና ዲሞክራሲ ወዴት አለ?

በአስፋው ጌታቸው (የገበያና ቢዝነስ ደቨሉፕመንት አማካሪ) 12



## አንድ በሉ

በዚህ አምድ ስር ሀገራዊ የፖለቲካ ጉዳዮች ይዳሰሳሉ

# ሲኖዶሱ እና መጅሊሱ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ማጥመቂያ?



ተመስገን ደሳለኝ

ጳጳሳት፣ ካህናት፣ ቀሳውስት፣ ዲያቆናት፣ ሼህ፣ ኢማም፣ ኡላማ፣ ደረሳ፣ ፓስተር፣ ዘማሪ፣ ካድሬ፣ ጠርናፊ፣ ተጠርናፊ፣ ሊግ፣ ማህበር፣ ፎረም፣ ግንባር ቀደም አርሶአደር፣ ልማታዊ ባለሀብት፣ ልማታዊ ጋዜጠኛ፣ ልማታዊ አርቲስት፣ ልማታዊ ማስታወቂያ ሰራተኛ፣ ልማታዊ እድር፣ ልማታዊ ማህበር፣ ልማታዊ... ማን ቀረ? ማንም:: እናም በዛሬ ጊዜ እመንም አትመንም የእነዚህ ሁሉ ምንጭ መለስ እና ኢህአዴግ ናቸው። በተቀረ የእምነት/ሀይማኖት መገኛ ቤተክርስቲያን እና መስጊድ መሆናቸው ከቀረ ዘመን አልፎበታል። ስብከትም ሆነ ዝማሬ አሊያም ዝየራ ከመፃሀፍ ቅዱስና ከቅዱስ ቁራን ሳይሆን አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከተሰኘው እስታሊናዊ መፀሀፍ ነው። መምህሩም አንድ እሳቸው «ዘላለማዊው» ናቸው። ከዚህ ውጭ ለሲኖዶሱም ሆነ ለመጅሊሱ እየሱስና ነብዩ፣ ወይም ሙሴና ሙሳ ቦታ የላቸውም። ሆኖም በዚህ ቅር አትሰኝ፣ ምክንያቱም ለአብዮታዊ ዲሞክራሲና ለ«ሰውየው» ገለታ ይድረሳቸውና አብዮታዊያን «ሙሴ» እና «ሙሳ»ን አዘጋጅተውልኻል።

**ዕፅመ-ታሪክ**

እንዲህም ይጀምራል፡- ከዕለታት አንድ ቀን ጠረፍ ጠብቁልን ያልናቸው ወታደሮች ተሰባሰቡና መንግስት መሰረቱ። የተመሰረተው መንግስትም ምድራዊ አይደለምና ሊተች፣ ሊነቀፍ፣ የስራ ማቆም አድማ ሊደረግበት፣ የተቃውሞ ሰልፍ ሊወጣበት... አይገባም ሲሉ አዋጅ አወጁ። አዋጁም እንዲህ እንደዛሬው መወንጀያ ከመሆኑ በፊት «የኢትዮጵያ ትቅደም አላማን የሚቃወም...» በሚል የሚጀምር «አማላይ» እንደነበር ወደዚንባቤ ጎራ ብለህ ማረጋገጥ ትችላለህ። ምናልባትም ዚንባቤ የሚርቅህ ከሆነ በቅርቡ ከእስር የተፈቱትን «የቀድሞ ትናንሽ አማልክት»፣ የደርጉ መስራች ባለስልጣናትን ፈልገህ ጠይቃቸው «ተፀፅቼአለሁ» ብለዋልና ሳይደብቁ ይነግሩሀል።

የሆነ ሆኖ ባለፈው መንግስት ውስጥ የነበረው «ሀይማኖት»አንድ ነው። መጠሪያውም «ሶሻሊዝም» የተሰኘ ሲሆን አማልክቱም ከፍ ሲል ሌኒንና ጓደኞቹ፤ ዝቅ ሲል መንግስቱ ኃ/ማርያምና ግብረ አበሮቹ ነበሩ። በተረፈ እግዚአብሔር፣ አላህ፣ ኢየሱስ፣ ቡድሃ፣ ባዒ... ጂኒ ቁልቋል በ1967ቱ አዋጅ ተሽረዋል። መሻራቸውንም ተከትሎ መቀጣጫ ይሆን ዘንድ ከጳጳሳቱ፣ ከሼሁ፣ ከፓስተሩ ተመርጠው መስዋዕት ሆኑ። ከዚህ በኋላም እውነት እውነት እልሀለው ለ17 አመታት ያህል ምድሪቱን ሞልተዋት የነበሩት መንጌ እና ጓደኞቻቸው ብቻ ነበሩ።

እነሆም ይህ ከስጋም ከነፍስም የተጣላው የመንግስቱ ኃ/ማርያም መንግስት በመለስ ዜናዊና ጓደኞቻቸው ብርቱ ትግል፤ተራራ መውጣትና መውረድ (ማንቀጥቀጥም) ተጨምሮበት፣ እንዲሁም የእነአሞራውና የእነቾቺ ገብሩ መስዕዋትነት ታክሎበት እንዳይሆን እንዳይሆን ሆኖ ወደቀ። ከውድቀቱ በኋላም በአዋጅ የተሻረው ፈጣሪ በህገ-መንግስት ተመለሰ ተባለ። እነሆም ስለፈጣሪ መመለስ የተበሰረበት ህግ ምዕራፍና ቁጥር፡-

***«ማንኛውም ሰው የማሰብ፣ የህሊናና የሃይማኖት ነፃነት አለው። ይህ መብት ማንኛውም ሰው የመረጠውን ሃይማኖት ወይም እምነት የመያዝ የመቀበል፤ ሃይማኖትና እምነቱን ከሌሎች ጋር በመሆን ወይም ለብቻው በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣ የመከተል፣ የመተግበር፣ የማስተማር ወይም የመግለፅ መብትን ያካትታል።» (የኢፌዴሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 11፣ ንዑስ አንቀጽ 1)***

በእርግጥም አሸናፊዎቹ ባለጎፈሬ ታጋዮች የሃይማኖት ነፃነትን በተመለከተ ይህንን ብቻ አይደለም በህግ የደነገጉት። ሌላም አላቸው፤ በግልፅ እንዲህ የሚል፡-

***«በአንቀጽ 90 ንዑስ አንቀጽ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የሃይማኖት ተከታዮች ሃይማኖታቸውን ለማደራጀት፣ ለማስፋፋት የሚያስችላቸውን የሃይማኖት ትምህርት፣ የአስተዳደር ተቋም ማቋቋም ይችላሉ» (የኢፌዴሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 11፣ ንዑስ አንቀፅ 2)***

መቼም ይሄ እፁብ ድንቅ አዋጅ ነው። ያውም ራሳቸውን የምድር አማልክት ባደረጉ ወታደሮች የተመሰረተ መንግስት በወደቀ ማግስት የተሰማ አዋጅ! ግና ምን ዋጋ አለው! «ነበር ባይሰበር» ሆነ እንጂ? («ነበር ባይሰበር»ን ወደታች እናየዋለን)

...ከዚህ ቀደም ደግመን ደጋግመን እንድተነጋገርነው ደርግና ኢህአዴግ በአፈፃፀም እንጂ በአካሄድ ፍፁም የተለያዩ ናቸው። ደርግ አንጻ ግራንጻ አያበዛም፣ ዴሞክራሲ፣ ነፃ ፕሬስ፣ ሰብዓዊ መብት፣ ሰማያዊ መብት... ቅብርጥሶ የሚባል «ግርዶሽ»ም የለውም፤ ወይም አይፈልግም። ምክንያቱም ደርግ «ነፍሴ» ምንም ይሁን ምን መቀበል እንጂ መቃወም እንደማይቻል በግልፅ «እኛ ወታደሮች ነን ደማችን ቶሎ ይፈላል» ብሎሃልና። እንደአየሽውና እንደሰማሽውም ህዝባዊ መንግስት፣ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የሃይማኖት ነፃነት... ያሉ ሀገር ወዳዶች፣ ሀገር ወዳድ ነን ባሉ ወታደሮች እንደወጡ ቀርተዋል።

ኢህአዴግ «ነፍሴ» ጋ ስትመጣ ግን ይኼ የለም። ሲጀመርም የኢህአዴግ ልጆች ወታደሮች አይደሉም-ታጋዮች ናቸው። በቃ! ታጋይ ማለት አንተ ስትራብ አብሮ የሚራብ (በእርግጥ አመራሩ ለረሃብተኛ የመጣ ስንዴን፣ ረሃብተኛው እንደቅጠል ቢረግፍም ሽጦ ጠመንጃ ከመግዛት አይመለስም። ይሄ ግን ሁልጊዜ አይደለም። አልፎ አልፎ ነው፣ ሁልጊዜማ ዕርዳታም የለ)፤ ብቻ ታጋይ ማለት ድርጅትን እንጂ መሪውን የማያመልክ፣ የማያንቆለጳጵስ (የዛሬን አያድርገውና) ነው። የትኛውም ታጋይ በበረሃ ቆይታው ያለውን ችግር ፊት ለፊት ይናገር ነበር። መለስም ላይ እንኳ ቅሬታ ቢኖረው «ተጋዳሊ መለስ...» ብሎ ሳይፈራና ሳይሽማቀቅ በግምገማ ይተቻቸዋል። በረከት ስምኦንንም ሆነ አዲሱ ለገሰንም እንዲሁ ታጋዩ እኩል ምክንያት ጠቅሶ ይከራከራል። ይህ የሆነው ለምን መሰለህ? ታጋዩ እርሻውንም ሆነ ትምህርቱን ትቶ የተሰባሰበው «የተጨቆኑ ህዝቦች» አሉ ተብሎ ሲነገረው «ነፃ ላውጣ» በሚል ስለሆነ ነው። በተቀረ ማንንም ጠይቅ ወይም የትግሉን ታሪክ (ሚዛናዊ ሆነው የተፃፉትን) አንብብ ያ ሁሉ ኢትዮጵያዊ ከቤቱ የወጣው አንተና እኔን ስልት በቀየረ አዲስ ጨቋኝ ለመጨቆን አልነበረም።

የሆነ ሆኖ ኢህአዴግ እና መለስ ወይም መለስ እና ኢህአዴግ የሃይማኖት ነፃነት አውጀዋል አልኩህ እንጂ በሃይማኖት ጣልቃ አይገቡም አላልኩህም። እንዲህማ ልልህ አልችልም። እንዴትስ እልሃለሁ? ለምሳሌ እነ መለስ ደርግን አሸንፈው አዲስ አበባ ሲገቡ ከበረሃ ይዘው የመጡት የብሔር ፖለቲካ እና በቋንቋ ላይ የተመሰረተውን የፌዴራሊዝም ስርዓት ብቻ አይደለም። ለኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታዮች «ፓትርያርክ»ም ይዘውላቸው ነው የመጡት። ያውም ዶ/ር ብፁእ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስን።

በእርግጥ እኚህ ብፁእ አባታችን «እግዚአብሔር የለም» በሚለው ደርግ ወደእስር ቤት ተወርውረው ምድራዊ መከራን ተቀብለዋል፤ ሆኖም ይህ ብቻውን ከእምነቱ ቀኖናና ዶግማ (Dogma) ውጭ በሆነ ሁኔታ «እግዚአብሔርም አላህም ከወዴትም አይደለም፣ ከሰማይም አይደሉም፣ ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ እንጂ» በሚለው እምነት የለሹ ኢህአዴግ ፓትርያርክ ሆነው ሊያሾማቸው አይችልም። ነገር ግን ተሾመዋል-ጊዜው የአሸናፊዎች ነውና። መቼም የአቡኑ ወደመንበሩ መምጣት ከኢህአዴግ ጋር መያያዙ አከራካሪ ጉዳይ አይመስለኝም። በእርግጥ ማስረጃ የሚፈልግ ዊክሊክስን መንብኘቱ ብቻ በቂ ነው። አዎን! በወቅቱ የኢህአዴግ ሁለተኛ ሰው፣ በዚህ ዘመን ደግሞ «ፓስተር» የሆኑት ታምራት ላይኔ ለአሜሪካው አምባሳደር ዶናልድ ቡዝ «እኛ ከጫካ አዲስ አበባ ስንገባ በስልጣን ላይ የነበሩት ፓትርያርክ አቡነ መርቆርዮስ ከስልጣናቸው እንዲባረሩ የተደረጉት በእኔ ፊርማ ነው» ሲሉ የእምነት ክህደት ቃላቸውን ሰጥተዋልና።

በዚህ ብቻ የሚገታ እንዳይመስልህ የአባታችንና የፓርቲያችን ፍቅር፤ ምክንያቱም «የግንቦት 20 ፍሬ» የሆኑት አቡነ ጳውሎስ ከእምነቱ ተከታዮች እና ከአንዳንድ ጳጳሳት የሚደርስባቸውን ተቃውሞ ሁሉ እያፈኑ እና እየደፈጠጡ እዚህ የደረሱት በማን ድጋፍ ይመስልሃል? መቼም «ሚካኤል በሰይፉ ጠብቋቸው ነው» እንደማትለኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ሌላው ቢቀር ድህረ ምርጫ 97ን ተከትሎ የተነሳውን ተቃውሞ አስታኮ በ1998 ዓ.ም. የጥምቀት በዓል ሲከበር፤ ሾላ አካባቢ የሚገኘውን የካ ሚካኤል ያጀቡ ምዕመናኖች የዘመሩትን መዝሙር ትረሳዋለህ ብዬ አላስብም። ምንአልባት ማስታወሱ አስፈላጊ ከሆነም መዝሙሩ ይኸው፡-

«ጳጳሱ ፌዴራል ናቸው
ሚካኤል ፍረድባቸው»

እሺ! እንግዲያስ ብፅዑ ወቅዱስነታቸውን ሚካኤል ካልጠበቃቸው የጠበቃቸው አንድ ሀይል አለ ማለት ነው። እናም እኔ እልሃለሁ እመነኝ ያ ሀይል የአብዮታዊ ዴሞክራሲ እንጂ የሌላ የማንም አይደለም። ለምሳሌ ሰኔ 29 ቀን 2001 ዓ.ም. ጀምሮ «በስም» ከፓትርያርኩም ስልጣን በላይ እንደሆነ የሚነገርለት «ሲኖዶሱ» ጠቅላላ ጉባኤውን አድርጎ ነበር። የእድል ጉዳይ ሆኖም በዛ ጉባኤ አቡነ ጳውሎስ ስልጣን ከያዙ ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሲኖዶሱ ሰምተውት የማያውቁት ብርቱ ተቃውሞ ቀረበባቸው። በወቅቱም ስለነበረው ሁኔታ አዲስ ነገር ጋዜጣ የሰራውን ዜና እንደወረደ ላቅርብልህ፡-

«ለሳምንታት በውዝገብ ውስጥ የቆየው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ አስቸኳይ ጉባኤው ትናንት አርብ ሐምሌ 10 ቀን ከሰዓት በኋላ ተጠናቀቀ። ጉባኤው ለዚህ ሳምንት ከተያዙለት አጀንዳዎች ብዙዎቹን አልተመለከታቸውም። ፓትርያርኩ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ላይ የጣሉትን እገዳ ሲኖዶሱ ማንሳቱ የተገለጠ ሲሆን ፓትርያርኩ ከአስተዳደር ስራ እንደወጡ ቀርቦ የነበረው ሀሳብ ሳይነሳ ቀርቶ ፓትርያርኩ በነበሩበት ሁኔታ ቀጥለዋል» ይልና የጋዜጣው ዘጋቢ ሶኖዶሱ እዚህ ውሳኔ ላይ የደረሰበትን ምክንያት እንዲህ ሲል ያቀርበዋል። «ጉባኤው ሐሙስ ጠዋት ይመለከተዋል ተብሎ የነበረው አጀንዳ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ረዳት ሊቀ ጳጳስ አቡነ ሳሙኤልን ጉዳይ ነበር። ይህን አጀንዳ እያስላሰሉ ወደየማረፊያቸው ከተበታተኑት ጳጳሳት አምስቱ ግን ሌሊቱን ያሳለፉት እንዳሰቡት አልነበረም። ረቡዕ ምሽት ከ4፡00 ጀምሮ አምስቱ ሊቃነ ጳጳሳት ያልጠበቋቸውን እንግዶች ለማስተናገድ መገደዳቸውን ለጳጳሳቱ ቅርብ የሆኑ ምንጮቻችን ገልፀዋል። በውዝግቡ ሰሞን የሲኖዶሱ ጊዜያዊ ስብሳቢ ሆነው ተመርጠው የነበሩት ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ማረፊያ ቤት ባልታወቁ ሰዎች መገንጠሉን የቤተ ክህነቱ ምንጮች አረጋግጠዋል። ማንነታቸው ያልታወቁት ሰዎች በአካባቢው በተሰማው ድምፅ ጳጳሱ ወደነበሩበት ውስጠኛ ክፍል ሳይገቡ መሄዳቸውን ብፁዕነታቸው ለፖሊስ በሰጡት ቃል ማረጋገጣቸውንም እነዚሁ ምንጮች ተናግረዋል። የብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ እና የብፁዕ አቡነ ፋኑኤል ቤቶች በሮችም መደብደባቸውንና የማስጠንቀቂያ ንግግሮች ከውጭ መሰማታቸውን ለጳጳሳቱ ቅርብ የሆኑ ምንጮች ባለቤቶቹን ዋቢ በማድረግ ይናገራሉ። በሌላ በኩል ብፁዕ አቡነ ኤጲፋንዮስ እና የሥራ አስፈፃሚው አባል የሆኑት ብፁዕ አቡነ መልከፃዴቅ ግን መታወቂያ አሳይተውናል ባሏቸው ሰዎች ከቤታቸው ተወስደው መመለሳቸውን የሲኖዶሱ ምንጮች አረጋግጠዋል።» ብላለች «አዲስ ነገር» ጋዜጣ።

መቼም እነዚያ ዛሬም ድረስ ቢሆን ማንነታቸው ያልታወቁ ሰዎች በር የገነጠሉት መቋሚያና ፅናፅን ታጥቀው እንዳይመስልህ። ወይም ሁለቱን ጳጳሳት «መታወቂያ በማሳየት» የወሰዷቸው ግለሰቦች ያሳዩአቸው መታወቂያ የቲዎሎጂ (የመንፍሳዊ ኮሌጅ) መታወቂያ ነው የሚል ቀልደኛ ይኖራል ብዬ አላስብም። እናም ደግሜ ደጋግሜ እጠይቃለሁ። ከዚህ በላይ የሃይማኖት ጣልቃ ገብነት ማለት ምን ማለት ነው? እመነኝ ይህ አይነቱ አሰራር በሁሉም ሃይማኖት የሚተገበር ነው። ...ሌላ ተጨማሪ መረጃ ለማቅረብ ያህል በነገስታቶቹ ይገፋና ይገለል የነበረው የኢትዮጵያ ሙስሊም ወንድምና እህቶቻችንን ጉዳይ እንየው።

ለመጀመሪያ ጊዜ «ኃይማኖት የግል ነው፤ አገር ግን የጋራ ነው» ያለው ነጋድራስ ገብርህይወት ባየከዳኝ እንደነበረ ይነገራል። አፄ ኃ/ስላሴም ተቀብለው አስተጋቡት፣ ሆኖም በእሳቸው ፀናላቸው። እኔም እስልስዋለው ኢትዮጵያና ሌሎች ነብያት ያላቸውን ትስስር ያህል፣ ኢትዮጵያና ነብዩ መሀመድም አላቸው። እናም ኢትዮጵያዊ ለመባል በምድሪቷ መወለድ እንጂ የአንድ ሃይማኖት ተከታይነት በፍፁም ቦታ የለውም። ኢትዮጵያ የማንም አይደለችም-ከኢትዮጵያውያኖች በቀር። የማንም ወደብም፣ ደሴትም፣ ባህርም አይደለችም።

ለዚህም ነው የአወሊያ ተማሪዎችን ጥያቄ ተከትሎ በርካታ ሙስሊሞች ኢማም፣ ሙአዚን፣ ሙፍቲ፣ ኡላማ፣ ዳኢ፣ ደረሳ፣ ኡስታዝ፣ ሀጂ፣ ሼኽን.... ከቁራን እንጂ ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ አንቀበልም ሲሉ በየጁማው ህብረ-ድምፃቸውን እያሰሙ ያሉት።

የእስልምና እምነት ተከታዮች ጥያቄ ሲጨመቅ እንዲህ የሚል ሆኖ ታገኘዋለህ፡- መጅሊሱ (የእስልምና ጠቅላይ ጉዳዮች ም/ቤት) የሚመሰረተው በሙስሊም ምዕምናን ምርጫ ብቻ ነው። ወይም ስልጣን ላይ ያለውን መጅሊስ አንፈልገውምና ይውረድ ሊባል የሚችለው በሙስሊሙ እንጂ በዶ/ር ሽፈራው ኃ/ማርያም አሊያም በኩማ ደመቅሳ ፍላጎት አይደለም። በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ «አህባሽ» የሚባል የእስልምና አስተምህሮትን «ተቀበል»፣ «አልቀበልም» በሚል በመጅሊሱና በምዕመናኑ መካከል የከረረ ውዝግብ ተፈጥሮ እያየን ነው። የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትርም የአንድ «ኡላማ»ን ያህል ስለ አህባሽ እስላማዊነት እየሰበኩ እንደሆነ እየሰማን ነው። ለምሳሌ በሐምሌ 2003 ዓ.ም. በሐረር ሐረማያ ካምፓስ በፌዴራል ጉዳዮችና በመጅሊስ ትብብር በተዘጋጀው «የአህባሽ» ስልጠና ላይ ዶ/ር ሽፈራው እንዲህ አሉ፡-

«ከመጅሊሱ እውቅና ውጪ የሚፈፀሙ ድርጊቶች ይቁሙ ብላችሁ ያቀረባችሁት አለ። ሼክ አህመዲን የሚያነሱት እንደተጠበቀ ሆኖ በኛ በኩል ከፍቃድ ውጪ የሚደረግ ትምህርት፣ ዳዕዋ፣ ስብከት፣ ከፈቃድ ውጪ የሚሰሩ መድረሳዎች፣ ከፈቃድ ውጪ የሚሰሩ መስጊዶች፣ ከፈቃድ ውጪ የሚሰሩ ኹጥባዎች ሁሉ መቆም አለባቸው ነው የምንለው»

የተከበሩ ሚኒስትር ለዳዕዋ እና ስብከት ፈቃድ ጠይቁኝ ማለታቸው በእጅጉ አስቂኝ

ወደ ገፅ 6 ዞሯል »

ኤድናሞል
ሳምንቱን ሙሉ
ይታያል
አለም ሲኒማ
ማክሰኞ 10:00
ቅዳሜ ምሽት 2:30
እሁድ 10:00
ሴባስቶፖል
ማክሰኞ 10:00
ሐሙስ 5:00
ቅዳሜ 8:00
እሁድ 8:00
ዮፍታሔ
ሰኞ 10:00
እሁድ 10:00 እና 12:00
እምቢልታ
ሰኞ 10:00
ረቡዕ 12:00
ሐሙስ ምሽት 2:30
እሁድ 8:00
አጐና ሰራዊት
ሰኞ 10:00
ማክሰኞ 8:00
ሐሙስ 10:00
እሁድ 12:00
ካፍደም
ሳምንቱን ሙሉ
ይታያል
ዋፋ
(ቴድምሮስ አደባባይ)
ማክሰኞ 12:00




ሴፍ (ቡራዩ)
10:00 እና 12:00

ኅሕ መፅሄት

**ዋና ስራ አስኪያጅ**
ልዑል ቀስቅስ

**ዋና አዘጋጆች**
ደሳለኝ አዴላ ገብሬ

**General Manager**
Leul Keskis

**Editors in Chief**
Dessalegn Adella Gebre



## የሰማዩን እንኳ ተዉልን!!

ለመጀመሪያ ጊዜ ‹‹ኃይማኖት የግል ነው፤ አገር ግን የጋራ ነው›› ያለው ነጋድራስ ገብርህይወት ባየከዳኝ እንደነበረ ይነገራል፡፡ እና የሃገሬ ሰው ይሄንኑ ሲል ነው የኖረው ኢትዮጵያና ሌሎች ነብያት ያላቸውን ትስስር ያህል፣ ኢትዮጵያና ነብዩ መሀመድም አላቸው፡፡ እናም ኢትዮጵያዊ ለመባል በምድሪቷ መወለድ እንጂ የአንድ ሃይማኖት ተከታይነት በፍፁም ቦታ የለውም፡፡ ኢትዮጵያ የማንም አይደለችም-ከኢትዮጵያውያኖች በቀር፡፡ ለዚህም ነው የአወሊያ ተማሪዎችን ጥያቄ ተከትሎ በርካታ ሙስሊሞች ኢማም፣ ሙአዚን፣ ሙፍቲ፣ ኡላማ፣ ዳኢ፣ ደረሳ፣ ኡስታዝ፣ .... ከቁራን እንጂ ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ አንቀበልም ሲሉ በየጁማው ህብረ-ድምፃቸውን እያሰሙ ያሉት በዚህም ምክንያት ነው መሪዎቻቸው የታሰሩት፡፡ የእስልምና እምነት ተከታዮች ጥያቄ ሲጨመቅ እንዲህ የሚል ሆኖ ታገኘዋለህ፡-መጅሊሱ (የእስልምና ጠቅላይ ጉዳዮች ም/ቤት) የሚመሰረተው በሙስሊም ምዕምናን ምርጫ ብቻ ነው፡፡ ወይም ስልጣን ላይ ያለውን መጅሊስ አንፈልገውምና ይውረድ ሊባል የሚችለው በሙስሊሙ እንጂ በዶ/ር ሽፈራው ኃ/ማርያም አይደለም፡፡ በተለይም ከ1ዓመት በፊት ጀምሮ ‹‹አህባሽ›› የሚባል የእስልምና አስተምህሮትን ‹‹ተቀበል››፣‹‹አልቀበልም›› በሚል በመጅሊሱና በምዕመናኑ መካከል የከረረ ውዝግብ ተፈጥሮ እያየን ነው፡፡ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትርም የአንድ ‹‹ኡላማ››ን ያህል ስለ አህባሽ እስላማዊነት እየሰበኩ እንደነበርም የሰማንው ነው፡፡

የሆነ ሆኖ ባለፈው የደርግ መንግስት ውስጥ የነበረው ‹‹ሀይማኖት››አንድ ነው፡፡ መጠሪያውም ‹‹ሶሻሊዝም›› የተሰኘ ሲሆን አማልክቱም ከፍ ሲል ሌኒንና ጓደኞቹ፤ ዝቅ ሲል መንጌና ግብረ አበሮቹ ነበሩ፡፡ በተረፈ እግዚአብሔር፣ አላህ፣ ኢየሱስ፣ ቡድሃ፣ ባሂ... ጂኒ ቁልቋል በ1967ቱ አዋጅ ተሽረዋል፡፡ መሻራቸውንም ተከትሎ መቀጣጫ ይሆን ዘንድ ከጳጳሳቱ፣ ከሼሁ፣ ከፓስተሩ ተመርጠው መስዋዕት ሆኑ፡፡ ከዚህ በኋላም ለ17 አመታት ያህል ምድሪቱን ሞልተዋት የነበሩት መንጌ እና ጓደኞቻቸው ብቻ ነበሩ፡፡

እነሆም ይህ ከሲጋም ከነፍስም የተጣላው የመንግስቱ ኃ/ማርያም መንግስት በመለስ ዜናዊና ጓደኞቻቸው ብርቱ ትግል፤ ተራራ መውጣትና መውረድ ተጨምሮበት፣ እንዲሁም የእነቾቪ ገብሩ መስዕዋትነት ታክሎበት እንዳይሆን እንዳይሆን ሆኖ ወደቀ፡፡ ከውድቀቱ በኋላም በአዋጅ የተሻረው ፈጣሪ በህገ-መንግስት ተመለሰ ተባለ፡፡ እነሆም ስለፈጣሪ መመለስ የተበሰረበት ህግ ምዕራፍና ቁጥር፡- ‹‹ማንኛውም ሰው የማሰብ፣ የህሊናና የሃይማኖት ነፃነት አለው፡፡ ይህ መብት ማንኛውም ሰው የመረጠውን ሃይማኖት ወይም እምነት የመያዝ የመቀበል፤ ሃይማኖትና እምነቱን ከሌሎች ጋር በመሆን ወይም ለብቻው በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣ የመከተል፣ የመተግበር፣ የማስተማር ወይም የመግለፅ መብትን ያካትታል፡ ›› (የኤፌዴሪ ህግ-መንግስት አንቀጽ 11፣ ንዑስ አንቀጽ 1)በእርግጥም ኢህአዴጎች የሃይማኖት ነፃነትን በተመለከተ ይህንን ብቻ አይደለም በህግ የደነገጉት፡፡ ሌላም አላቸው፤ በግልፅ እንዲህ የሚል፡-
‹‹በአንቀጽ 90 ንዑስ አንቀጽ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የሃይማኖት ተከታዮች ሃይማኖታቸውን ለማደራጀት፣ ለማስፋፋት የሚያስችላቸውን የሃይማኖት ትምህርት፣ የአስተዳደር ተቋም ማቋቋም ይችላሉ›› (የኢፌዴሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 11፣ ንዑስ አንቀፅ 2)

ይህን ስልህ ታዲያ ኢህአዴግ የሃይማኖት ነፃነት አውጅዋል አልኩህ እንጂ በሃይማኖት ጣልቃ አይገቡም አላልኩህም፡፡

ለምሳሌ እነ መለስ ደርግን አሸንፈው አዲስ አበባ ሲገቡ ከበረሃ ይዘው የመጡት የብሔር ፖለቲካ እና በቋንቋ ላይ የተመሰረተውን የፌዴራሊዝም ስርዓት ብቻ አይደለም፡፡ ለኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታዮች ‹‹ፓትርያርክ››ም ይዘውላቸው ነው የመጡት፡፡ ያውም ዶ/ር ብፁኡ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስን፡፡ በእርግጥ እኒህ ብፁኡ አባታችን ‹‹እግዚአብሔር የለም›› በሚለው ደርግ ወደእስር ቤት ተወርውረው ምድራዊ መከራን ተቀብለዋል፤ ሆኖም ይህ ብቻውን ከእምነቱ ቀኖናና ዶግማ ውጭ በሆነ ሁኔታ ‹‹እግዚአብሔርም አላህም ከወዴትም አይደለም፣ ከሰማይም አይደሉም፣ ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ እንጂ›› በሚለው እምነት የለሹ ኢህአዴግ ፓትርያርክ ሆነው ሊያሾማቸው አይችልም፡፡ ነገር ግን ተሾመዋል-ጊዜው የአሸናፊዎች ነውና፡፡ መቼም የአቡኑ ወደ መንበሩ መምጣት ከኢህአዴግ ጋር መያያዙ አከራካሪ ጉዳይ አይመስለኝም፡፡ በወቅቱ የኢህአዴግ ሁለተኛ ሰው፣ በዚህ ዘመን ደግሞ ‹‹ፓስተር›› የሆኑት ታምራት ላይኔ ለአሜሪካው አምባሳደር ዶናልድ ቡዝ ‹‹እኛ ከጫካ አዲስ አበባ ስንገባ በስልጣን ላይ የነበሩት ፓትርያርክ አቡነ መርቆርዮስ ከስልጣናቸው እንዲባረሩ የተደረጉት በእኔ ፊርማ ነው›› ሲሉ የእምነት ክህደት ቃላቸውን ሰጥተዋልና፡፡

እናም በዛሬ ጊዜ እመንም አትመንም የእነዚህ ሁሉ ምንጭ መለስ እና ኢህአዴግ ናቸው፡፡ በተቀረ የእምነት/ሀይማኖት መገኛ ቤተክርስቲያን እና መስጊድ መሆናቸው ከቀረ ዘመን አልፎበታል፡፡ ስብከትም ሆነ ዝማሬ አሊያም ዝየራ ከመፃህፍ ቅዱስና ከቅዱስ ቁራን ሳይሆን አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከተሰኘው እስታሊናዊ መፀሀፍ ነው፡፡ መምህሩም አንድ እሳቸው ‹‹ዘላለማዊው›› ነበሩ አሁንም ከሰማይ ቤተ ሆነው ሳያስተምሩን አይቀርም፡፡ ከዚህ ውጭ ለሲኖዶሱም ሆነ ለመጅሊሱ እየሱስና ነብዩ፤ ወይም ሙሴና ሙሳ ቦታ የላቸውም፡፡ ሆኖም በዚህ ቅር አትሰኝ፣ ምክንያቱም ለአብዮታዊ ዲሞክራሲና ለ‹‹ሰውየው›› ገሊታ ይድረሳቸውና አብዮታዊያን ‹‹ሙሴ›› እና ‹‹ሙሳ››ን አዘጋጅተውልኻል፡፡

ህገ-መንግስቱን የተመለከትከው ጊዜ ኢህአዴግ እንዴት እየቀለደበት እና እንዴት እንደ መሸወጃ እየተጠቀመበት እንደሆነ ሲገባህ የራሱን የኢህአዴግን ጤነኛነት ያጠራጥርሃል ጤነኛ ያልሆነ ድርጅት ደግሞ ሀገር ሲመራ ሀገሪቷን ይዞ ወደ ገደል ላለመግባቱ ምንም ማስተማኛ የለውም፡፡

**Dessalegn Adella Gebere**
**Bayreuth**

## ኤልሳ መንግስቱ አበራ

የተከበራችሁ ለኢትዮጵያ ነፃነት አንድነት ብልፅግናና ለኢትዮጵያ ሉአላዊነት ለምትፋለሙ ለምትታገሉና ድጋፍ ለምታደርጉ ንፁህ ኢትዮጵያውያን በቅድሚያ የእግዚአብሔር ሰላምታ አቀርባለሁ፡፡

ከላይ በጠቀስኩት መልክ ይህ ፅሁፍ ያነጣጠረው ህውሀት /ኢፒአርዲፍ/ አባላትንና የሱ ደጋፊዎች ለሆኑ አገር አጥፊዎችና ቅጥረኞችን የሚመለከት ሲሆን ይህ የኔ አመለካከት ብቻ ሳይሆን አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ሀሳቤን ይጋራል ብዬ አምናለሁ፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ ግንቦት 7/1997 ቅንጅትን ሲመርጥ በግምትና በቅዠት አይደለም ምክንያት አለው ወያኔን ያለምንም ድጋፍ በ0 /ዜሮ/ እንዲሸነፍ ያደረገው በ3 የተለያየ አስተዳደር ሳይሆን የግፍ አገዛዝ ብዙ ትምህርት ያገኘበት በመሆኑ ለአንዴም ለመጨረሻ የግፍ አገዛዙን ምዕራፍን ለመዝጋት ነበር የምርጫ ካርዱን የተጠቀመበት፡፡ ነገር ግን የበግ ለምድ የለበሰው ወያኔ ለምዱ ኢፒአርዲፍ እርቃኑን ቀረ፡፡

በመጨረሻም በኤፕሪል 13 2013 ላይ እነ ልዑል ቀስቅስ የሰሩት ድራማ እጅግ አሳዛኝም አሳፋሪም ሆኖ ስላገኘሁት እነሆ ላካፍላችሁ ወደድሁ።

ከስደተኞች የአባልነት መዋጮና የምዝገባ እያሉ ገንዘብ መሰብሰብ ሳያንሳቸው የታዋቂ ግለሰቦችን ፅሑፍ በመስረቅ ጭምር ጥራዝ በማሳተምና አባላትን በ10 ዩሮ ካልገዛችሁ በማለት ዝርፊያ የሚያካሂዱት ጭንጋፍ /ምቱር/ ፖለቲከኞች በኤፕሪል 13-2013 ዓ.ም በኑረንበርግ ከተማ የድግስ ፕሮግራም አዘጋጁ።ማዘጋጀታቸው ባልከፋ ግን **ለዚህ ድግስ ማዘጋጃ ስደተኞች ሃምሳ፣ሃምሳ /50/ ዩሮ አዋጡ ተባሉ፤ " ከድግሱ ሽያጭ ስናተርፍ ገንዘባችሁ ይመለሳል" በሚል ሥላቅ!!!**እጅግ አሳዛኙ ነገር ደግሞ **የድግሱን ምግብና ቢራ እንዲገዙ የተፈረደባቸው እኒያው መከረኛ ስደተኞች መሆናቸው ነው፤ያውም የመኖሪያ ፈቃድ ለማግኘት ያለሥራ በተስፋ የጀርመን መንግስትን ምላሽ የሚጠብቁ ምስኪን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን!!!**

*(ውድ አንባቢያን! ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ ጥቂት ስለ ጀርመን የስደተኞች ህግ ይህን ልበል፦የጀርመን የኢሚግሬሽን ህግ ከሌሎች የምዕራብ ሀገራት ብዙም የሚለይ ባለመሆኑ ማንኛውም የፖለቲካ ጥገኝነት የጠየቀ ሰው ያሳለፈው የፖለቲካ ህይወት ወይም አሁን እያደረገ ያለው የፖለቲካ ተሳትፎ ከግምት ይገባል።ለዚህም ሲባል በርካታ ኢትዮጵያውያን አማራጭ በማጣታቸው በነዚህ ጭንጋፍ /ምቱር/ ፖለቲከኞችና ፍሬ-አልባ ድርጅቶቻቸው ወጥመድ ውስጥ ይገባሉ።)*

የእናት ሆድ ዥንጉርጉር እንዲሉ በተመሳሳይ ቀንና ሀገር በሙንሽን /ሚዩኒክ/ ከተማ በዚሁ በጀርመን የሚገኝ የሲቪክ ድርጅት በቅርቡ ከቤኒሻንጉል ክልል በተፈናቀሉ የአማራ ተወላጆች ላይ የደረሰውን የዘር ማጽዳት በመቃወም የጀርመን መንግስት ለወያኔ መንግስት እርዳታ እንዳያደርግ ጀርመናውያን በፊርማቸው እንዲያረጋግጡ ከበርካታ ጀርመናውያን ፊርማ ሲያሰባስብ ውሏል።ወላድ በድባብ ትሂድ ነበር ያሉት አበው።

# ማጠቃለያ

"ለምጣዱ ሲባል፥አይጧ ትለፍ" የሚባል የጥንት አባባል አለ።ነገር ግን አሁን አይጧ ራሷ ምጣዱን እየሰበረችው ነው!!!አይጧ የጭንጋፍ /ምቱር/ ፖለቲከኞች ተምሳሌት ስትሆን ምጣዱ ግን በስደት የሚገኙ የመኖሪያ ፈቃድ ለማግኘት ሲሉ በነዚህ ፍሬ-አልባ ድርጅቶች መዳፍ የወደቁ ምስኪን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ናቸው።ከነሱም ባሻገር ደግሞ የሀገራችንና የህዝቦቿ ጉስቁልና ያሳስበናል።በግሌ አንድ ሃሳብ እንደመፍትሔ ይታየኛል።እነዚህ ስደተኞችን ለፍርድ ቤቶች በሚጠቅማቸው መንገድ ቀድሞ ይገኙበት በነበረው የድርጅት ቦታ ተስተካካይ የሆነ ቦታ (ሥልጣን) ተመቻችቶላቸው ከጭንጋፍ /ምቱር/ ፖለቲከኞች መዳፍ እንዲወጡ በማድረግ እንዲሁም ሌሎች የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲን ያቀፈ፣እውነተኛ ራዕይ ያለውና በሀገራችን የፖለቲካ ለውጥ ላይ የራሱን ሚና መጫወት የሚችል የፖለቲካ ድርጅት ማቋቋምና መምራት የሚችሉ ሰዎች ጉዳዩን ቢያዩት እነዚህ ጭንጋፍ /ምቱር/ ፖለቲከኞችንና ፍሬ-አልባ ድርጅቶቻቸውን መነጠልና እርቃናቸውን ማስቀረት ብሎም በግፍ የተገነባውን የገቢ ምንጫቸውን ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲነጥፍ በማድረግ በፖለቲካችንና በህዝባችን ላይ

የሚያደርሱትን ጠባሳ እና በስደተኛ ወንድሞቻችን ላይ የሚያደርሱትን በደል ለዘለቄታው ማስቆም ይቻላል።

በዚህ አጋጣሚ በነዚህ ፍሬ-አልባ ድርጅቶች ውስጥ "ስልጣን" ተሰጥቷቸው የመኖሪያ ፈቃድ ለማግኘት ሲሉ ላይ ታች የሚባክኑ ወንድሞቻችንንና እህቶቻችንን ጉዳይ ከግምት ሳያስገቡ እነዚህን ድርጅቶች በጭፍኑ ለማፍረስ የሚደረግ ሩጫ በወንድሞቻችን ቁስል ላይ ጥዝጣዜን መጨመር ብቻ ሳይሆን ግለኝነትን የሚያንፀባርቅና ነገም እንደአሁኖቹ ጭንጋፍ /ምቱር/ ፖለቲከኞች ላለመሆን ዋስትናን የማይሰጥና ኢ-ሰብዓዊና ኢትዮጵያዊ ጨዋነት የጎደለው ተግባር ነው።በአጭር ጥናት በግሌ ለማረጋገጥ እንደቻልኩት እነዚህ ላይ ታች የሚባክኑ የመኖሪያ ፈቃድ የሌላቸው ወንድሞች እውነተኛ የፖለቲካ ድርጅት አግኝተውና የፍርድ ቤት ጉዳያቸውን በማያበላሽ መልኩ ቀድሞ በነበራቸው ቦታ ተመጣጣኝ ቦታ ቢሰጣቸው የሐሰት ሐዋሪያ ሆነው የጭንጋፍ /ምቱር/ ፖለቲከኞች መጠቀሚያ ሆነው መቀጠል እንደማይፈልጉ አረጋግጠውልኛል።

በነገራችን ላይ በጀርመን ስላሉ ሌሎች ጭንጋፍ /ምቱር/ ፖለቲከኞችና ፍሬ-አልባ ድርጅቶቻቸው እንዲሁም ብቅ ብቅ እያሉ ስላሉት ዞምቢዎች በቀጣዩ ክፍል አቀርባለሁ።በቸር ያቆየን!!!

**ኢትአርየነ እግዚኦ ሙስና ኅበ ኢትዮጵያ!!!**

**አቤቱ የኢትዮጵያን ጥፋት አታሳየን !!!**

## ሠላማዊት አሰፋ

## ሚዩኒክ ጀርመኒ